**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ**

Solidarity Movement for a New Ethiopia

# ዶ/ር ሙሃመድ ሻምሳዲን ሜጋሎማቲስ - የቀበሮ ባህታዊ!

እኛ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ውስጥ የምንገኝ ይህንን ጽሁፍ እንድናወጣ ያስገደደን ዋናው ነገር በርዕሱ ስሙ የተጠቀሰው ግለሰብ በተደጋጋሚ የሚያወጣቸው ጥላቻን የተሞሉና ከፋፋይ ጽሁፎች መቆም እንዳለባቸው ለማስገንዘብ እና ሕዝባችን የዚህን ግለሰብ ማንነት ተረድቶ አቋም እንዲወስድ ለማሳሰብ ነው፡፡ ይህ ግለሰብ በኢትዮጵያ የሚገኙ የአንድን ብሔር አባላት የሚደግፍ መስሎ በመቅረብ በአጠቃላይ በኢትዮጵዊነት ላይ ግን የጥላቻ መርዝ የሚረጭ ብቻ ሳይሆን በብሔሮች እንዲሁም በሃይማኖቶች መካከል ግጭት እንዲፈጠርና ይህም ወደከፍተኛ መተላለቅ እንዲቀየር ቀን-ተሌት የሚለፋ ነው፡፡ የዚህን ግለሰብ አሸባሪ አቋም ለሚመለከታቸው ዓለምአቀፋዊ ድርጅቶች እንዲሁም ለፌዴራሉ የምርመራ ቢሮ (Federal Bureau of Investigation – FBI) ሪፖርት የምናደርግ ሲሆን ሕዝባችን ይህንን ጉዳይ በአንክሮ ተመልክቶ የሚገባውን ድርሻ እንዲወጣ አደራ ጭምር እናሳስባለን፡፡

ይህ የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላት የሆነ ግለሰብ በትውልዱ የግሪክና የቱርክ ዝርያ ያለው ሲሆን ባሁኑ ጊዜ ግብጽ እንደሚኖር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ዕድሜው 36 እስኪደርስ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ የነበረ ሲሆን ከዚያ በኋላ ወደእስልምና የተቀየረ መሆኑ ይነገራል፡፡ አድናቂዎቹ የበርካታ መጽሐፍት ደራሲና ‹‹ፕሮፌሰር ፤ ዶክተር›› እያሉ ቢጠሩትም ግለሰቡ ብዙ ጊዜውን ኢትዮጵያን የሚከፋፍል እና ሕዝቦቿን እርስበርስ የሚያጋድል ትናንሽ መጣጥፍ በማውጣት እንደሚያሳልፍ የራሱ ጽሑፎች ምስክር ናቸው፡፡ እነዚህም በተለይ በኦሮሞዎች፣ በኦጋዴኖችና በሌሎች ወገኖች ላይ ያተኮረና ለሰብዓዊ መብታቸው የሚሟገት ቢመስልም እንደ መፍትሔ አድርጎ የሚያቀርባቸው ነጥቦች ግን ሁልጊዜ በጥላቻ የተሞሉና ለበለጠ መከፋፈል የሚዳርጉ ከመሆናቸዉም ባሻገር ባጠቃላይ በምስራቅ አፍሪካ አካባቢ ቀውስ እንዲፈጠር የሚያበረታቱ ናቸዉ፡፡

በቅርቡ በተከታታይ በኦሮሞዎች ላይ ያወጣቸውን እና በተለያዩ ድረገጾች (the American Chronicle, Buzzle.com and Ethiopian News at Google.com) ላይ የታተሙት[1] ጽሁፎች የዘር ማጥፋትን፣ የሃይማኖት ግጭቶችን፣ የሰብዓዊ መብቶችን ረገጣ የሚቃወም ማንኛውም ግለሰብም ሆነ ድርጅት የዚህን ግለሰብ ጽሑፎች እንዲያወግዝና ድረገጾቹም ጸሑፎቹን በሙሉ እንዲያስወግዱ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡ ለዓብነት ያህል ይህ ግለሰብ ባለፈው የሐምሌ ወር ብቻ ለኦሮሞ ህዝብ ያለውን ‹‹ፍቅር›› የገለጸ በሚመስልበት ሁኔታ 22 መጣጥፎች ያወጣ ሲሆን በእነዚህ ጽሁፎች የአማራውን ብሔር ‹‹አውሬ›› እያለ በመጥራት ሥር የሰደደ ጥላቻን የሚያበረታቱ ከመሆናቸዉም በላይ በዚሁ ሐምሌ ወር ባወጣቸው ሌሎች 34 ጽሁፎቹም አገራችንን - የውሸት ኢትዮጵያ ("Fake Ethiopia") እያለ በመጥራት በብሔረሰቦች መካከል

---

[1] http://news.google.com/nwshp?client=firefox-a&rls=org.mozilla:en-US:official&hl=en&tab=wn

ንቀት፣ መጠላላትና መገዳደል የሚያበረታታ ለመሆኑ ሥራዎቹ በግልጽ ይመሰክራሉ፡፡ ለማስረጃም ያህል በሐምሌ ወር ካወጣቸው ጽሁፎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸዉ።

- Oromos Reject the CIA-Imposed Invitation of Freemason, Zionist Ambassador Shinn in OSA Conference *July 27, 2010*
- Keep Terrorist Berhanu Nega Out of OSA Conference & Put a Tombstone on Fake Ethiopia, Oromos Demand *July 24, 2010*
- Committed to Continuing the Ethiopian Genocides, Berhanu Nega Has No Place in an Oromo Conference *July 23, 2010*
- Overwhelming Oromo Reaction Against CIA-planned Amharization of OSA: No to Racist Ethiopianist Dogma
- OLF and Oromos Incompatible with Amhara Racist Ethio-fascist Opposition Ginbot, Kinijit, SMNE *July 16, 2010*
- Fake Ethiopia Cannot Be United: the Abyssinian Elites´ Barbarism Rejected by Subjugated Nations VI *July 14, 2010*
- Irreconcilable Gap Heralding the End of Fake Ethiopia: Oromo Culture vs. Abyssinian Barbarism V *July 13, 2010*
- Nile Politics: Tyrannized Oromos Side with Egypt to Break Down Habesha State of Fake Ethiopia II *July 07, 2010*
- Nile Politics: Tyrannized Oromos Prefer Egypt, Being Ready to Let Fake Ethiopia Drop Dead *July 07, 2010*
- Egypt and Sudan Concerned with Oromos Reaching out for Support against Abyssinia (Fake Ethiopia) *July 02, 2010*

ይህ ግለሰብ ምንም እንኳን ኦሮሞዎችን፣ ኦጋዴኖችን እና ሌሎች የተጨቆኑ ብሔሮችን የሚደግፍ መስሎ በመታየት የአብዛኛዎቹን ድጋፍ ለማግኘት ቢጥርም፤ ዋና ዓላማው ግን ኢትዮጵያ ተብላ የምትጠራ አገር እንዳትኖርና ሕዝቦቿ እርስበርስ እንዲጨራረሱ የማድረግ ድብቅ ዓላማ ያለው ነው፡፡ በዚሁ ዓመት ባለፈው ወር ይኸው ግለሰብ በድረገጾች ላይ በበተነው ጽሁፍ ኦሮሞ ወገኖቻችን ከሱዳን ጋር እንዴት መተባበር እንዳለባቸው አስመልክቶ እንደሚከተለዉ ጽፏል።[2]

> *“ኦሮሞች እና የኦሮሞ ነጻ አውጪ ግምባር (ኦነግ) ይህንን እየተራባ የመጣውን ‹በአማሮችና በኦሮሞዎች መካከል ውይይት እየተደረገ ነው› እየተባለ የሚወራውን አሉባልታና ቁሻሻ ሃሳብ ፈጽሞ መቃወም አለባቸው፡፡ . . . ከዚህ በተጨማሪ ኦሮሞዎችና ኦነግ ኦሮሚያን ነጻ ሊያወጣ የሚችል ተግባራዊ ዕቅድ በአስቸኳይ ካልነደፉ ለሚመጣው ችግር ተጠያቂዎች እንደሚሆኑ ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ የኦጋዴን ነጻ አውጪ ግምባር (ኦብነግ) እና ኦሮሞዎች በአንድነት ሆነው ከሱዳን ጋር ትብብር መመሥረት አለባቸው ፤ ከዚያም ነጻነታቸውን ከተጎናጸፉ በኋላ ከሱዳን ጋር በመዋሃድ ከግብጽ ድንበር አንስቶ እስከ ሶማሊያ የሚደርስ አንድ ታላቅ የኩሽ መንግሥት መመሥረት አለባቸው፡፡”*

የዚህን ግለሰብ ፅሁፎች ጥንቅቆ ለተረዳ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በምስራቅ አፍሪካም አለመረጋጋትን ብሎም የዘር መጠላላትና መተላለቅ እንዲከሰት የሚያበረታታ ለመሆኑ ማስረጃ ነው፡፡ ይህም ተግባሩ ሂትለር በአይሁዳውያን ላይ ካደረሰው የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲሁም በሩዋንዳ ከደረሰው የዘር ዕልቂት ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ይህንን አስመልክቶ ለሚደርስ ማናቸውም ነገር ይህንን ግለሰብ በራሱ ጽሁፎች ተጠያቂ ማድረግ እንደሚቻል እሙን ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ከፉፉይ አጀንዳ ያነገበ ግለሰብ በታሪካዊ ጠላታችን ግብጽ ወይም ሱዳን

---

[2] http://www.americanchronicle.com/articles/view/169704 OLF and Oromos Incompatible with Amhara Racist Ethio-fascist Opposition Ginbot, Kinijit, SMNE, by Dr. Muhammad Shamsaddin Megalommatis, July 16, 2010

ወይም ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድ እንዳይሆኑ ቀን ተሌት በሚተጋው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ድጋፍ የሚሰጠው ሆድ-አደር ስለመሆኑ የሚጠቁሙ ሌሎች መረጃዎችም አሉ፡፡

እንደሚታወቀው ወደ ግብጽና ሱዳን ከሚፈሰው የአባይ ወንዝ 85 በመቶ ያህሉን የምታበረክተው ኢትዮጵያ ናት፡፡ እናም ሱዳንና ግብጽ ጠንካራና የተባበረች ኢትዮጵያ እንዳትመሠረት በማድረግ በአባይ ወንዝ አጠቃቀም ላይ ያላቸውን የበላይነት ጠብቀው ለመኖር ፍላጎት እንዳላቸው የማይካድ ሃቅ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ይኸው ጸረ ኢትዮጵያ የሆነ ግለሰብ በአንድ ወቅት ሲጽፍ *‹‹አሸባሪ የሆነችውን አቢሲኒያ (የውሸት ኢትዮጵያ) የአባይን አጠቃቀም በተመለከተ በግብጽና ሱዳን ላይ የሃሰት ውንጀላ እያደረሰች በመሆኗ በምስራቅ አፍሪካ አካባቢ ያለውን ጸጥታ እያናጋች የምትገኝ ቁጥር አንድ አሸባሪ በመሆኗ ይህችን አገር በፍጥነት መገነጣጠልና ማፈራረስ ለአካባቢው መረጋጋት የተሻለ መፍትሔ የሚያመጣ ነው››* [3]ብሏል፡፡

በዚህ ኢትዮጵያን በማፈራረስ ጉዳይ ላይ የዚሁ ግለሰብ ደጋፊ የሆነው ፊሊፔ ሂልበርግ የተባለ በኒውዮርክ ከተማ የሚገን ጃርክ ካፒታል የተባለ ድርጅት የቦርድ ሊቀመንበር የሆነ ሌላ ሆድአደር ከደቡብ ሱዳን ክልል 400,000 ሄክታር መሬት በሊዝ የወሰደ ሲሆን በ2000 ዓም ከፋይናንሺያል ታይምስ ጋር ባደረገው ቃለምልልስ *‹‹የተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ናይጄሪያን እና ኢትዮጵያን ጨምሮ በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የሚበታተኑ መሆናቸውን››* እንደሚያምን የገለጸ ሲሆን *‹‹በአሁኑ ጊዜ እሱ እየተጋፈጠ ያለው የፖለቲካና የሕግ አደጋ (risk) እነዚህ አገሮች በሚበታተኑበት ጊዜ ትልቅ ሽልማት እንደሚሆነው››* ጠቅሷል፡፡ ሲቀጥልም ለዚሁ እንዲረዳው በዳርፉር፣ በኢትዮጵያ እንዲሁም በሶማሊላንድ ከሚገኙ የአማጺያን ኃይላት (ነጻ አውጪ ግንባሮች) ጋር ግንኙነት እንደሚያደርግ በንግግሩ መግለጹን ጽሁፉ ያትታል፡፡[4] [5]

በተለያዩ ጊዜያት የመተባበር ወይም የአንድነት ጉዳይ ከኢትዮጵያውያን መካከል ሲነሳ የዚሁ ሜጋሎማቲስ የተባለ ግለሰብ ከፋፋይና ጸረ አንድነት ጽሁፍ Google Ethiopian News እና የዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል ድረገጾችን ማጣበብ ይጀምራል፡፡ ከዚህም አኳያ ካየነው የዚህን ግለሰብ አጀንዳ ከበስተጀርባ ሆነው የሚያራምዱ ኃይላት የውጪ ብቻ ሳይሆኑ በአገራችን ላይ ለሁለት ዓስርተ ዓመታት የጭቆና መረቡን ዘርግቶ የሚገኘው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ እንደሆነ ድርጊቶቹ ራሳቸው እማኝነት ይሰጣሉ፡፡

ከሁለት ዓመታት በፊት የንቅናቄያችን መሪ የሆኑት አቶ ኦባንግ ሜቶ የዚህ ግለሰብ የጥቃት ዒላማ እንደነበሩ በተለያዩ ድረገጾች ላይ ግለሰቡ ባወጣቸው ጽሁፎች የተወሳ ነበር፡፡[6] አቶ ኦባንግ ከ 1995-1998 ባሉት ዓመታት የአኙዋክ ሕዝቦች ላይ የደረሰውን ጭፍጨፋ አስመልክቶ የአኙዋክ የፍትሕ ጉባዔ የሚባል ድርጅት አቋቁመው ይሠሩ በነበሩበት ወቅት ግለሰቡ ለድርጅቱም ሆነ ለአቶ ኦባንግ ድጋፍ ያደርግ የነበረ ሲሆን ከዓመታት በኋላ ግን አቶ ኦባንግ ሌሎች ኢትዮጵያውያን በማቀፍ ኅብረብሔራዊ ንቅናቄ (ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ) መሥርተው መንቀሳቀስ በጀመሩበት ወቅት ይኸው ግለሰብ የቀድሞ ድጋፉን በማቋረጥ በተቃራኒው ከፍተኛ የሆነ የጥላቻና የነቀፋ ብሎም ጉዳዩን የግል በማድረግ አጸያፊ፣ ተራ እና

---

[3] Keep Terrorist Berhanu Nega Out of OSA Conference & Put a Tombstone on Fake Ethiopia, Oromos Demand; July 24, 2010; http://www.americanchronicle.com/articles/view/171505

[4] U.S. investor believes Ethiopia likely to break apart soon; January 19th, 2009; Financial Times; by Javier Blas and William Wallis

[5] Fragmenting Sudan—the Jarch Way; March 9,2009, http://szamko.wordpress.com/2009/03/06/fragmenting-sudan-the-jarch-way/

[6] "A Pseudo-Christ for 'Ethiopia': the 'Reverend' Moon, the Amharas and Obang Metho": "Obang Metho and the besotted Amharas, the racist imbeciles of Kinijit and Ginbot-7, want to replace Zenawi, and most probably, if they achieve it, they will find themselves as East Africa's puppets of Sun Myung Moon, the Pseudo-Christ." http://www.buzzle.com/articles/a-pseudo-christ-for-ethiopia-the-reverend-moon-the-amharas-and-obang-metho.html : (http://www.americanchronicle.com/articles/72790 ) http://www.buzzle.com/articles/obang-metho-fake-christianity-unveiled-korean-funds-behind-him.html

መሠረተ ቢስ የሆኑ ጽሁፎች መጻፉን ተያይዞት ነበር፡፡ ይህም ሳያንሰው በተለያዩ ጊዜያት አቶ አበበ ገላውን እና አቶ ኣብርሃ በላይን እንዲሁ ሲዘልፍ ቆይቶ አሁን በቅርብ ጊዜ ደግሞ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን፣ አቶ ጃዋር ሲራጅ ሞሐመድን እንዲሁም የቀድሞ አምባሳደር የሆኑትን ዴቪድ ሺንን ባለፈው ወር በሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ በተካሄደው የኦሮሞ ጥናት ማኅበር ተካፋይ በመሆናቸው ከፍተኛ የሆነ የጥላቻ፣ የነቀፋና ተራ የስድብ ጽሁፎችን በተከታታይ ሲጽፍ ቆይቶ ነበር፡፡

ስለ ዶ/ር ብርሃኑ የጻፈው እንዲህ ይነበባል፡-

> *ብርሃኑ ነጋ የተባለው ዘረኛ፣ አፍቃሪ ኢትዮጵያ፣ ጸረዴሞክራትና ከፋፋይ እንዲሁም ማንቦት 7 የተባለ የአማራ ዘረኛ ፖለቲካ ፓርቲ አባል የኦሮሞን ህዝብ ከምድረገጽ ለማጥፋትና የተቀሩትን ደግሞ አቢሲኒያ በተባለችው (የውሸት ኢትዮጵያ) ሥር በጭቆና እንዲማቅቁ ለማድረግ ቁርኝነቱን ገልጧል፡፡ . . .*
> *በጣም የሚያሳዝነው ጉራጌዎችም የኦሮሞ እና የሌሎች የኩሽ ዝርያ ያላቸው ጠላት የሆነውን የአማራን መንገድ ለመከተል መወሰናቸው ነው፡፡ በነጻዪቱ ኦሮሚያ አናሳ ሆነው መኖር ለመቀበል ያልፈለጉት ጉራጌዎች ከአማራ ወራሪዎች ጋር ያልተቀደሰ ስምምነት ለማድረግ መወሰናቸው ሌላው አሳዛኝ ሁናቴ ነው፡፡ እነዚህ ጉራጌዎች ከአንድ ክፍለዘመን በላይ ከፋፋይ፣ ዘረኛ፣ ክፉ እና ፍጹም ሠይጣናዊ የሆነውን ‹‹ኢትዮጵያ›› የተባለውን ፕሮጀክት ለማስፈጸም እና የተቀሩትን በመደምሰስ፣ በማዋረድ፣ ከምድረገጽ በማጥፋት፣ በማዋሃድ እና በመቀላቀል ላይ በተመሰረተ የአማራ የበላይነት ሥር ለመሆን ፈቃደኛነታቸዉን ገልጸዋል . . . እንዲያውም እነዚህ ጉራጌዎች ምንም ዓይነት አስተሳሰብ የሌላቸው ከንቱ ከመሆን አልፈው ‹‹ኢትዮጵያ›› ተብላ ለምትጠራ ዘር አጥፊ ማሽን ዋጋ የሌላቸው ሸቀጥ ሆነዋል፡፡ እንዲያውም ጉራጌ የሚባል ሕዝብ የሌለ ብቻ ሳይሆን አለን የሚሉትም ጥቂቶች ያልሰነጠኑ እና የራሳቸውን ማንነት በቅጡ ለመረዳት የማይችሉ ኋላ ቀሮች ናቸው፡፡* [7]

በዶ/ር ብርሃኑ ላይ ይህንን ከማለቱ በተጨማሪ የኦሮሞ ወገኖቻችንን አስመልክቶ የሚከተለዉን ዓይነት ጽሁፍ አቅርቦም ነበር፡-

> *ማንኛውም ዓይነት ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ከሚያራምድ ድርጅት ጋር የሚደረግ ድርድር የኦሮሞን ብሔራዊ ማንነት አደጋ ላይ የሚጥል ብቻ ሳይሆን የኦሮሞን ሕዝብ ማንነት የሚያጠፋም ነው፡፡ እያንዳንዱ የኦሮሞ አርበኛ ራሱን ከሌሎች ጋር በማስተባበር እነዚህን የኦሮሚያን ምድር የሚያቆሽሹ ወንጀለኛ አውሬዎችን ከምድረገጽ ለማጥፋት የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ አለበት፡፡እያንዳንዱ አፍቃሪ ኢትዮጵያ የሆነ ሁሉ ከናዚ ጀርመን ወታደር የባሰ ዘረኛ ስለሆነ ጥይት በግምባሩ ብቻ ነው የሚገባው፡፡ . . . ኦሮሚያን ነጻ ለማውጣት እንደ ብርሃኑ ነጋ ዓይነት ወንበዴ ሁሉ ከኦሮሚያ እንዲርቅ ወይም እንዲሞት ብቻ ነው መደረግ ያለበት፡፡ . . . ጥቂት አፈንጋጭ ኦሮሞዎች እና ኢትዮጵያዊ አጀንዳ የሚያራምዱ ሃሰተኛ ምሁራን የሆኑ ሁሉ የአእምሮ በሽተኞች ስለሆኑ ሊወገዙ እና ከማንኛውም በኦሮሚያ ከሚገኝ ጥቅም ሊወገዱ ይገባል፡፡ . . . እንዲያውም ቀዳሚ ተግባር ሊሆን የሚገባው እነዚህን ሃሰተኛ የምሁር ቁሻሻዎችን ማስወገድና የአማራን የበላይነት ከምድረገጽ በማጥፋት የኦሮሞን ሕዝብ ለማይቀረው ድል ማዘጋጀት ነው፡፡*[8]

---

[7] Committed to Continuing the Ethiopian Genocides, Berhanu Nega Has No Place in an Oromo Conference: July 23, 2010 ; http://www.americanchronicle.com/articles/view/171325

[8] Overwhelming Oromo Reaction Against CIA-planned Amharization of OSA: No to Racist Ethiopianist Dogma; July 22, 2010; http://www.americanchronicle.com/articles/view/171063

ንቅናቄያችን ከተለያዩ ኢትዮጵያውያን ጋር ካለው ግንኙነት በመነሳት ኦሮሞ ወገኖቻችንና የኦሮሞ ድርጅቶች እንዲህ ዓይነቱ መስመር የለቀቀና ከፋፋይ አስተሳሰብ ያራምዳሉ ብሎ አይገምትም፡፡ እንዲያውም እንደዚህ ዓይነቱን እነርሱን ለመርዳት አስመስሎ የቀረበ ነገር ግን በእነርሱ ለመጠቀም የሚፈልግ ወንጀለኛን ቀደመዉ ያጋልጣሉ ብሎ ያምናል፡፡ ለኦሮሞዎች ችግር መፍትሔ ጠቋሚዉ እንዲህ ዓይነቱ ከፋፋይና የኦሮሞን ሕዝብ ማንነት በቅጡ ያልተረዳ ግለሰብ ሳይሆን ራሳቸው ኦሮሞዎች ሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር መበተባበር በሚያደርጉት ዉይይት ነዉ፡፡ ብርሃኑ የኛ ነው፣ ጃዋርም የኛ ነው፡፡ ጉራጌ የኛ ነው፣ ኦሮሞው፣ አማራው፣ ትግሬው፣ አፋሩ፣ አኙዋኩ፣ በርታው፣ አሞው፣ ኮንሶው፣ ከቺፖው፣ ኩሬው፣ ኩናማው፣ መጀንጂሩ፣ ሙርሲው፣ ናያንጋቶሙ፣ ኑዌሩ፣ ቅማንቱ፣ ሻቦው፣ ሲዳማው፣ ጸማዩ፣ ወላይታው፣ ሃዲያው፣ ካፊቾው፣ ጋሞው፣ ሐመሩ፣ የሙ፣ ወዘተ የኛ ነው፡፡ እኛ ራሳችን ችግራችንንም ሆነ መፍትሔውን ለይተን የማወቅ ግዴታ አለብን። ሌላ እኛን ለመርዳት መስሎ ሊከፋፍለን የሚፈልግ የቀበሮ ባሕታዊ አንፈልግም፡፡ ልክ እንደ አውራ ዶሮዎች ጠብ እኛ ስንጣላና ስንገዳደል ሌሎች እኛን እያዩ እንዲደሰቱብን መፍቀድ የለብንም፡፡ ንቅናቄያችን እንዲህ ዓይነቱን የጠላት አስተሳሰብ በጥብቅ እንዲያወግዙና እንዲቃወሙ በኢትዮጵያ ለሚገኙት ከ80 በላይ ብሔሮች ጥሪውን ያቀርባል፡፡ ድረገጾችም የዚህን ግለሰብ ጽሁፍ ከማስተናገድ እንዲታቀቡና እስካሁንም ያከማቹትን እንዲያስወግዱ ሕዝባችን እንቅስቃሴ ማድረግ እንዲጀምር እናስገነዝባለን፡፡ እንዲሁም የኦሮሞ ጥናት ማኅበር (OSA)፣ ኦነግ እንዲሁም ኦብነግ እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሌሎች ድርጅቶች እንዲህ ዓይነቱን በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የዘር ማጥፋት ወንጀልን የሚያነሳሳ ተግባርም ሆነ ጽሑፍ እንዲያወግዙ በአክብሮት ያሳስባል፡፡

እስካሁን ተከፋፍለናል ፤ እስካሁንም የጠላቶቻችን መሳቂያና መጠቀሚያ ሆነናል፡፡ ካሁን በኋላ ግን እርስበርሳችን በመደጋገፍ ፣ ‹‹**ከጎሣ ይልቅ ሰብዓዊነትን በማስቀደም**›› ለራሳችን ነጻነት ብቻ ሳይሆን ለሁላችንም ነጻነት እንታገል፡፡ ለራሳችን ችግሮች መፍትሔው ራሳችን ጋር ያለ መሆኑን ተገንዝበን ሊጠቅሙን የሚፈልጉ መስለው ሊጠቀሙብን ከሚፈልጉ የውስጥና የውጪ ኃይሎች ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን እንከላከል፡፡ ሁላችንም ለእያንዳንዳችን፤ እንዳንዳችንም ለሁላችን ዘብ እንቁም፡፡ ፈጣሪችንም ከእኛ ጋር ሆኖ ይርዳን፡፡

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ**
*****************************************************************************************************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ የንቅናቄውን የዕርቅ ግብረኃይል በ (reconciliation@solidaritymovement.org) ወይም ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

